# 3ኛ ክፍለጊዜ የ4ኛ ክፍል ውጤት
# የወላጆች መመሪያ

በማርከ መስጫ ወቅት 3፣ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክህሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

እባክዎ ያስታዉሱ፦ በ ኢታሊክስ የሚታዩት ክህሎት እና ጽንሰ-ሐሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ አልተመዘገበም።

## ሂሳብ

### አለካከና መረጃ

- እርቀት፣ የጊዜ ክፍተት/ርቀት፣ የፈሳሽ ነገር ይዘት/volumes፣ የእቃዎች ግዝፈት/ክብደት፣ እና ገንዘብ፣ ቀላል የክፍልፋዮችን ወይም አስርዮሽ ፕሮብሌም ማቃለልን ጨምሮ እና መለካት የሚያስፈልግ ፕሮብሌሞች ትልቅ መስፈሪያ/መለኪያ ከአነስተኛ መለኪያ እንደሚስተያይ እና የቃላት ፕሮብሌሞችን ለማቃለል አራቱን የሂሳብ መደቦች/ስሌቶች ተጠቀም/ሚ። ባለቁጥር - መስመር የመለኪያ ሚዛን/ስኬል ያለው ስዕሎችን በመጠቀም የተለካውን ብዛት አመልክት/ቺ።
- በምድብ/በአሃድ ክፍልፋዮች ውስጥ የመለካት ውሂብ/data የሚያመለክት ባለመስመር ንድፍ ሥራ/ሪ። ባለመስመር ንድፍ ላይ የቀረበውን ዓይነት ኢንፎርሜሽን በመጠቀም የክፍልፋዮችን የመደመርና የመቀነስ ፕሮብሌሞች አቃልል/አቃልይ። ለምሳሌ፦ ከነፍሳት ናሙናዎች ስብስብ ውስጥ ባለመስመር ንድፍ በመጠቀም ረዥሙን እና የአጭሩን ልዩነት በማግኘት ተርጉም/ሚ።

### ቁጥሮችና ግብረቶች - ክፍልፋዮች

- አንድ ክፍልፋይ ከሌላ ክፍልፋይ ጋር እኩል መሆኑን በሥዕላዊ የክፍልፋይ ናሙናዎች/ሞዴሎች በመጠቀም፣ ሁለቱም ክፍልፋዮች ተመሣሣይ መጠን ቢሆኑም ቁጥሩ እና ክፋዮቹ በመጠን እንዴት እንደሚለያዩ ጥንቃቄ በማድረግ አስረዳ/ጂ። ተመጣጣኝ ክፍልፋዮችን ለመለየት እና ለመፍጠር ይህንኑ መርህ ተጠቀም/ሚ።
- ሁለት ክፍልፋዮችን በተለያዩ ተካፋዮች እና በተለያዩ አካፋዮች የጋራ አካፋዮችን ወይም ተካፋዮችን በመፍጠር፣ ወይም ከአንድ ሞዴል/ቤንች ማርክ ክፍልፋይ ጋር እያመሳከርክ/ሽ አወዳድር/ሪ። $\frac{1}{2}$ ማወዳደር/ማነፃፀር ተቀባይነት/ዋጋ የሚኖረው ሁለቱ ክፍልፋዮች ወደ አንድ ሙሉ ቁጥር ሲጠቁሙ/ሲያመለክቱ ብቻ እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል። የማወዳደሪያ ውጤቶችን በእነዚህ ምልክቶች >, =, ወይም <, ማሳየት እና መደምደሚያዎቹን በሥዕላዊ ክፍልፋይ ሞዴል/ናሙና አረጋግጥ/ጪ።
- አንድ ክፍልፋይ ከ $\frac{a}{b}$ a > 1 እንደ ክፍልፋዮች ድምር መረዳት። $\frac{1}{b}$
  - ክፍልፋዮችን መደመር እና መቀነስ ማለት አንድ ሙሉ ነገር የሚያመላክቱ ክፍሎችን ማገናኘት/መገጣጠም እና ማለያየት/መከፋፈል እንደሆነ ተረዳ/ጂ።
  - አንድን ክፍልፋይ በተመሣሣይ አካፋይ ከአንድ አይነት በሚበልጥ አሠራር መነጣጠል፣ እያንዳንዱን ክፍልፋይ/ንጠላ በእኩልነት ምልክት (=) መመዝገብ። የተነጣጠሉትን በሥዕላዊ ክፍልፋይ ሞዴል/ናሙና አረጋግጥ/ጪ።
  - ድብልቅ ቁጥሮችን በአንድ ዓይነት አካፋይ ቁጥር መደመር እና መቀነስ፣ እያንዳንዱን ድብልቅ ቁጥር በተመጣጣኝ ክፍልፋይ በመተካት እና/ወይም በመደመርና በመቀነስ መካከል ያለዉን ግንኙነት እና የስሌቶችን ባህሪይ በመጠቀም።
- ክፍልፋዮችን አንድን ሙሉ ቁጥር በመጥቀስ እና በአንድ የጋራ አካፋይ፣ በመደመር እና በመቀነስ ፕሮብሌሙን ለመግለጽ ሥዕላዊ ክፍልፋይ ናሙና/ሞዴል እና የእኩልነት ምልክት (=) በመጠቀም የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት፡፡
- ክፍልፋይን በሙሉ ቁጥር ለማባዛት ቀደም ሲል የተረዳሃቸውን/የተረዳሻቸውን የብዜት ስሌት አስፍተህ/ሽ ተጠቀም/ሚ።
  - አንድን ክፍልፋይ ለመረዳት $\frac{a}{b}$ እንደ የ... ብዜት $\frac{1}{b}$ ለምሳሌ፣ ሥዕላዊ የክፍልፋይ ናሙና/ሞዴል ለመወከል ተጠቀም/ሚ $\frac{5}{4}$ ውጤቱን 5 X ($\frac{1}{4}$)፣ ማጠቃለያውን ውጤት በ እኩልነት ምልክት $\frac{5}{4}$ = 5 X ($\frac{1}{4}$) በመመዝገብ።
  - የ ብዜትን እንደ መረዳት/ማወቅ $\frac{1}{b}\frac{a}{b}$ እንደ ብዜት፣ እና ይህንን ግንዘቤ ክፍልፋይን በሙሉ ቁጥር ለማባዛት ተጠቀም/ሚ።
  - ሥዕላዊ የክፍልፋይ ናሙና/ሞዴል እና የእኩልነት/የይሆናል ምልክት (=) በመጠቀም ክፍልፋይን በሙሉ ቁጥር የማባዛት ቃላት ፕሮብሌም አቃልል/አቃልይ። ለምሳሌ፦ በአንድ ፓርቲ ላይ እያንዳንዱ ሰው ቢመገብ $\frac{3}{8}$ የአንድ ፓውንድ የተጠበሰ የበሬ ሥጋ፣ እና በፓርቲው ላይ 5 ሰዎች ቢኖሩ፣ ስንት ፓውንድ የተጠበሰ የበሬ ስጋ ያስፈልጋል?
- ባለ 10 እና ባለ 100 አካፋይ ያላቸዉ ሁለት ክፍልፋዮች እኩል መሆናቸዉን መግለጽ፣ እና ይህንኑ ዘዴ/ቴክኒክ ሌሎች ሁለት 10 እና 100 አካፋይ ቁጥር ያላቸዉ ክፍልፋዮችን ለመደመር ተጠቀም/ሚ። ለምሳሌ፦ ግለጽ/ግለጪ $\frac{3}{10}$ እንደ $\frac{30}{100}$ እና ደምር/ደምሪ $\frac{3}{10}+\frac{4}{100}=\frac{34}{100}$
- በ10 ወይም 100 አካፋይ ክፍልፋዮች አስርዮሻዊ/የዴሲማል ቅርጸት ሂሳብን ተጠቀም/ሚ። $\frac{62}{100}$ ለምሳሌ፦ 0.62 እንደገና ለመጻፍ እንደ፣ ርዝማኔውን እንደ 0.62 ሜትሮች ግለጽ/ጪ፣ 0.62 ን በቁጥር መስመር ስእል ላይ አሳይ።

### ስሌት እና የአልጄብራ አስተሳሰብ

- ከ1-100 ባሉት ቁጥሮች የሙሉ ቁጥሮችን አካፋይ ጥንዶች ፈልግ/ጊ። ሙሉ ቁጥር የራሱ አካፋይ ቁጥሮች ብዜት መሆኑን አስተውል/ይ። ከ1-100 ባሉት ቁጥሮች መካከል አንድ ሙሉ ቁጥር የአንድ - አሃዝ/ዲጂት/ብዜት ቁጥር መሆኑን/አለመሆኑን አረጋግጥ/ጪ። ከ1-100 ባሉት ቁጥሮች አንድ ሙሉ ቁጥር ብቸኛ ወይም ድብልቅ መሆኑን አረጋግጥ/ጪ።

## ምንባብ

### ስለ ምንባብ መረዳት፦ ስነ ፅሁፍ

- አንድ ጽሑፍ በቀም ነገር ምን እንደሚል በሚገለፅበት ጊዜ እና ከጽሑፍ ሃሳቦች በሚወሰዱበት ጊዜ በጽሑፉ የሚገኙ ዝርዝሮችና ምሳሌዎችን መጥቀስ።
- ከጽሑፍ ውስጥ የታሪኩን ጭብጥ/ፍሬሃሳብ፣ ድራማ፣ ወይም ግጥም ከዝርዝሮቹ በመለየት ማጠቃለያ አዘጋጅ/ጂ።
- በጽሑፉ ውስጥ በተወሰኑ ዝርዝሮች ላይ በማተኮር (ለምሳሌ፣ የገጸባህሪ ሃሳቦች፣ ቃላት፣ ወይም ድርጊቶች) የአንድ ታሪክ፣ ድራማ፣ ወይም ግጥም ገጸባህሪ፣መቼት፣ወይም ክዉነት በጥልቀት ማብራራት።
- በጽሑፉ ላይ የተጠቀሙበትን ቃላትና ሀረጎችን/አገላለጽ፣ በአፈታሪክ የሚጠቀሱትን ግዙፍ ባህርያት (ለምሳሌ፦ ግዙፉ .../ሄርኩሊን) ጭምር ትርጉማቸውን ወስን/ግለጽ/ግለጪ።
- በአንድ የትረካ ወይም ድራማ ጽሁፍ እና በጽሑፉ የቃል ወይም የፅሁፍ አቅርቦት መካከል ግንኙነቶችን መፍጠር፣እያንዳንዱ አቀራረብ በፅሁፍ ውስጥ የተወሰኑ ዝርዝር መግለጫዎችን እና አቅጣጫዎችን ዬት እንደሚያንፀባርቁ ለይቶ ማወቅ።
- ተመሣሣይ ጭብጥ/ፍሬሃሳብ እና ርእሶችን ይዘት (ለምሣሌ፦ የጥሩ እና የመጥፎ ተቃራኒነት) እና ስለክንውኖች ሥርአት (ለምሳሌ፦ ፈለግ) በታሪኩ ላይ ያለውን፣ አወራረድ/እንቅስቃሴ፣ እና የተለያዩ ባህላዊ ሥነ-ጽሑፎች ከተለያዩ ባህሎች አወዳድር/አወዳድሪ፣ አነፃጽር/አነፃፅሪ።
- በ4ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን አንብቦ መገንዘብ።

### ስለ ምንባብ መረዳት፦ መረጃያዊ

- የአንድን ፅሁፍ ዋና ሃሳብ መወሰንና በቁልፍ ዝርዝሮች እንዴት እንደሚደገፍ መወሰን፣ ፅሁፉን ማጠቃለል።
- ከፅሁፉ በሚገኝ የተለየ መረጃ ላይ በመመስረት፣ ክውነቶችን፣ ሂደቶችን፣ ሃሳቦችን ወይም ፅንሰሃሳቦችን በታሪካዊ፣ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ ፅሁፍ

ማብራራት፣ ምን እንደተካሄደ እና ለምንን ጨምሮ።

- ለ4ኛ ክፍል በሚመጥን አርእስት ወይም ትምህርት ላይ አጠቃላይ አካደሚ እና ጎራ-ተኮር ቃላት ወይም ሀረጎችን ትርጉም ለይተህ(ሽ) ግለጽ/ግለጪ።
- አጠቃላዩን መዋቅር ግለጽ/ጪ (ለምሳሌ:- ቅደምተከተል፣ ማወዳደር፣ ምክንያት/ውጤቱ፣ ችግሩ/መፍትሔው) የክስተቶቹ፣ ሃሳቦቹ፣ ፅንሰሃስቦቹ፣ ወይም በጽሑፉ ላይ ወይም በከፊል ጽሑፉ ያለው መረጃ።
- በቀጥታና በእጅ አዙር የተነገረን አንድ ተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ ማወዳደርና ማነፃፀር፤  ትኩረት የተደረገባቸውን ልዩነቶች እና የቀረበውን መረጃ መግለፅ።
- ጉዳዩን በትክክል አውቆ/ተረድቶ ለመፃፍ ወይም ለመናገር በአንድ አይነት ርእስ ከተጻፉ ሁለት ዓይነት መረጃዎችን/ኢንፎርሜሽን አገናዝብ/ቢ አቀናጅ/ጂ።
- ለ4ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነን መረጃያዊ ፅሁፍ ማንበብና መገንዘብ።

ቋንቋ:- የቃላት እውቀትና አጠቃቀም

- አንድ ተናጋሪ ልዩ ፍሬ ነገር ለመግለጽ የተጠቀማቸውን መደገፊያ ምክንያቶች እና መረጃዎችን ለይ።
- ያልታወቁ እና በርካታ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ሃረጎች በ4ኛ ክፍል ምንባብ ይዘት የተመሰረቱ፣ ከተደረደሩት ስልቶች እየተለዋወጡ በመምረጥ፣ ትርጉማቸውን መወሰን ወይም መግለጽ።
- የክፍል ደረጃን በትክክል የሚመጥን አጠቃላይ አካደሚያዊ እና ጎራ ተኮር የሆኑ ቃላት እና ሃረጎች፣ ትክክለኛ እርምጃዎችን የሚያካትት፣ ስሜታዊነትን፣ ለአንድ የተለየ ርእስ መሠረት የመሆን/የመገኘት/የመኖር አቋም (ለምሣሌ:- ስለ እንስሣት ጥበቃ ውይይት ሲደረግ የዱር አራዊት፣ ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ለአደጋ የተጋለጡ)ማግኘት እና መጠቀም።

## ጽሑፍ

ትምህርት ሰጭ/ገላጭ

- ርእሱን በግልጽ በማስተዋወቅ በአንቀጾቹ እና በክፍሎቹ መካከል ተመሣሣይ/ግንኙነት ያላቸው ሀሳቦችን አጣምር፣ የአቀራረብ/ይዞታን (ለምሳሌ:- የአርእስት አፃፃፍ)፣ ማሳያ/ለማብራሪያ የሚያገለግል፣ እና መረዳትን ለማገዝ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ ልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎችን  ጨምሮ።
- በመረጃዎች፣ ፍቺ፣ ተጨባጭ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ ወይም ሌላ ከርእሱ ጋር በሚገናኙ መረጃዎች/ኢንፎርሜሽን እና ምሳሌዎች ርእሱን አዳብር(ሪ)።
- በቀረበው ሀሳብ/ማብራሪያ ላይ የማጠቃለያ መግለጫ ወይም ክፍል ስጥ/ጪ።

ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር ውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክውነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካዎችን መጻፍ።
- ድርጊቶችን/ሁኔታዎችን ለማዛመድ የተለያዩ አገናኝ ቃላት እና ሀረጎችን ተጠቀም/ሚ።

ኣስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድን ርእስ ወይም ጽሁፍ ግልጽ በሆነ መንገድ ማስተዋወቅ፣ አንድ አስተያየት መግለጽ፣ እና የጸሐፊው(ዋ)ን ሃሳብ ለመደገፍ ተዛማጅ ሀሳቦች የተደረደሩበት ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።
- ቃላት እና ሀረጎችን በመጠቀም ሃሳብን እና ምክንያቶችን አገናኝ/ኚ( ምሳሌ:- ለምሳሌ፣ … ለማድረግ/… ለመሆን፣ በተጨማሪ)።
- ከቀረበዉ ሃሳብ/አስተያየት ጋር የሚዛመድ የማጠቃለያ /መደምደሚያ ዓረፍተነገር ወይም ክፍል አቅርብ/ቢ።

ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና ኣደረጃጀቱ ለተግባር፣ ኣላማ፣ እና ለኣድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮች እና ከትልልቅ ሰዎች ድጋፍ እና መመሪያ እያገኘህ(ሽ) እንደአስፈላጊነቱ፣ በማቀድ፣ ክለሳ በማድረግ፣ እና ለህትመት በማዘጋጀት ጽሑፍ አዳብር(ሪ)፣ እና አጠናክር(ሪ)።
- ከትልልቅ ሰዎች የተወሰነ አመራር እና ድጋፍ በማግኘት፣ ኢንተርኔትን ጭምር ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ጽሑፍን ለማዘጋጀት፣ ለማሳተም እና ከሌሎችም ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር፤ በአንድ ጊዜ ቢያንስ አንድ ገጽ በመፃፍ በቂ የኪቦርድ ችሎታ መካንህ(ሽ)ን አሳይ።
- የአንድ ርእስን የተለያዩ ገፅታዎች በመመርመር እውቀትን የሚገነቡ ኣጫጭር የምርምር ፕሮጀክቶችን ማከናወን።
- ከተሞክሮዎች ኣስፈላጊ መረጃዎች ማስታወስ ወይም ከህትመትና ከእሃዛዊ/digital ምንጮች ኣስፈላጊ መረጃዎች መሰብሰብ፤ ማስታወሻዎች መውሰድና መረጃዎችን መከፋፈል/በጎራ ማደራጀት፣ እና የምንጮች ዝርዝር መስጠት።
- ትንተና፣ ኣስተሳሰብ፣ እና ምርመራን ለመደገፍ ከስነፅሁፍ ወይም ከመረጂያዊ ፅሁፎች ማስረጃ መውሰድ።

የቋንቋ አጠቃቀም

- በአንድ ርእስ ወይም ጽሑፍ ሪፖርት ማድረግ፣ አንድ ታሪክ መንገር፣ ወይም አንድን ተሞክሮ በተደራጀ መንገድ መተረክ፣ ዋናዋና ሃሳቦችን ወይም ጭብጥ መልእክቶች ለመደገፍ በተገቢ ሃቆች፣ እና አስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፤ ተቀባይነት ባለው ፍጥነት በጥራት መናገር።
- በምትጽፍ(ፊ)በት ጊዜ ወይም በምትናገር(ሪ)በት ጊዜ የመደበኛ የእንግሊዝኛ ደንቦች የሰዋሰው/ግራመር እና አጠቃቀምህ(ሽ)ን ብቃት/ችሎታ አሳይ።
- ስትጽፍ/ፊ በመደበኛ የእንግሊዝኛ ደንቦች ትልቁን ፊደል መጠቀም፣ ስርአተ ነጥብ አገባብ/አጠቃቀም፣ እና የቃላት አፃፃፍ ችሎታ/ብቃት አሳይ።
- በእፃፃፍ፣ ኣነጋገር፣ በምንባብ፣ ወይም በማዳመጥ በቋንቋ እውቀት እና በህጎቹ መጠቀም።

## ሳይንስ

መሬትና የህዋ ሳይንሶች

- የቁስኣካልን እንቅስቃሴ በእፅዋት፣ እንስሶች፣ በብስባሾች/decomposers፣ እና በኣካባቢ ለመግለፅ ሞዴል ማዳበር።
- በምድር ላይ የውኃ ስርጭትን መረጃ ለመስጠት በተለያዩ የውኃ ማጠራቀሚያዎች/ማቆርያዎች ያለ ውኃ እና ንጽሕ ውኃ መጠን በግራፍ እና በመቶኛ ግለጽ/ጪ።
- የመሬትን ከባቢ አየር ሁኔታ እና ሃብት ለመንከባከብ እያንዳንዱ ሕብረተሰብ የሳይንስ አስተሳሰቦችን በምን ዓይነት መንገድ እንደሚጠቀሙ መረጃዎችን በማሰባሰብ አቀናጅ/ጂ።

## ማህበራዊ ጥናቶች

ባህል

- በሜሪላንድ ቀደምት ማህበረሰብን የተለያዩ ባህሎችን ግለጽ/ጪ።
- የህዝብና የቡድኖች አስተዋጽኦ በሜሪላንድ ሕብረተሰብ ላይ ምን ዓይነት/እንዴት ተፅዕኖ እንዳሳደረ ተንትን/ተንትኚ።
- በሜሪላንድ የተለያዩ ቡድኖችን (ህዝቦችን) ባህላዊ እንደምታዎች/ባህርያት ግለጽ/ጪ።
- በቅኝ ግዛት የነበሩ ማህበረሰቦችን በርካታ ባህሎችና ከባቢ ሁኔታ እንዴት ተፅዋ እንዳሳደረባቸው ግለጽ/ጪ።
- የአገሬው ህብረተሰብ በአሳሾቹ ሰፋሪዎች ልዩ ልዩ ባህሎች እንዴት እንደተሳቡ ትንታኔ አድርግ/ጊ።
- ከስደት፣ ከአሰፋፈር ሂደት/ሥርአት፣ እና የነዋየ ብልጽግና/እድገት በቅኝ ግዛቱ ላይ እንዴት ብዙሃነትን እየጨመረ እንደሄደ በትንታኔ አሳይ።
- በቅኝ ግዛት ዘመን በነበሩት ግንኙነቶች ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩትን ምክንያቶች ተንትን/ኚ።

ታሪክ

- በሜሪላንድ ቀደምት ሰፈራ ወደማድረግ የመሩትን  ቁልፍ የሆኑ ታሪካዊ ክስተቶችን የዘመን/የጊዜ ቅደምተከተልና አስፈላጊነት/ጠቀሜታ ተንትን/ኚ።
- ከአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት በፊትና በኋላ የሜሪላንድን አገር በቀል አሜሪካውያን ማህበረሰቦችን አወዳድር/ሪ።
- በቅኝ ግዛት አሜሪካ ቀደምት ሰፈራ ወደማድረግ የመሩትን  ቁልፍ የሆኑ ታሪካዊ ክስተቶችን የዘመን/የጊዜ ቅደምተከተልና አስፈላጊነት ተንትን/ኚ።

## መረጃዊ/ኢንፎርሜሽናል ማንበብ እና መጻፍ

- የመጠይቅ ሂደትን ተከተል/ይ እና ሂደቱን ከእውነተኛ ህይወት ጋር አገናኘው/ኚዉ።
- የኣንድን መረጃ ፍላጎት ለማሟላት ጥያቄዎችን ማስቀመጥና ማጣራት።
- መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ምንጮችን መርምር/ሪ።
- መረጃ ለማግኘት በተለዩ ምንጮች መገልገል።
- አሃዞችን/መረጃዎችን በተለያዩ ቅጾች መመዝገብ።
- ተፈላጊ መረጃን ለማሟላት የተቀረፀ/የተመዘገበ ውሂብ/መረጃ ጥራት መገምገም እና መተንተን።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።
- ለማጋራት የሚያስፈልጉትን መረጃ ግኝቶች/ እና ድምዳሜ ለማዘጋጀት የተለያዩ ቅርፀቶችን ይጠቀሙ።
- መገናኛ አውታር ላይ ሰላማዊ ተግባሮችን ተጠቀም/ተጠቀሚ።

## ስነጥበብ

### የሥነ-ጥበብ ፈጠራ እና ከሥነጥበብ ጋር ያለ ግንኙነት

- የመጀመሪያ፣ አዲስ የሚፈጠሩ፣ ያልተደባለቁ ሃሳቦችን ለማመንጨት የሚያነሣሱ ልዩ ልዩ ዓይነት የአቀራረብ ዘዴዎችን መርምር(ሪ)።
- ስለ ባህል በስእል/በቃላት ለማሳየት/ለመግለፅ የሥነጥበብ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆችን መርጠህ(ሽ) አደራጅ(ጂ)።
- የስነጥበብ መስሪያዎችን፣ ሚዲያ፣ እና የመሥሪያ ቦታን ስትጠቀም/ሚ ከባህላዊ/ልማዳዊ እና የፈጠራ ቴክኒኮች እና ልምምዶች ምረጥ(ጪ)።
- እየተሠራ ያለ የሥነጥበብ ሥራን ለማሻሻል እና የእጅጥበብ ሥራን ለማጣራት ግብረመልስ አስተያየትን ተግባራዊ አድርግ(ጊ)።
- የስነጥበብ ሥራ በመፍጠር ለባህላዊ ተለምዶ ምላሽ ስጥ(ጪ)።
- የሥነጥበብ ሥራው የተሠራበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ እና ባህል ኢንፎርሜሽን በመመርመር መረጃ ስጥ(ጪ)።

### የኪነጥበብ አቀራረብ እና የኪነጥበብ ግብረመልስ

- ለእይታ የሚቀርብ የሥነጥበብ ሥራ በመምረጥ ምርጫውን ከአርቲስቱ/ቷ(የኪነጥበብ ባለሙያ) ዐረፍተነገር ጋር አስረዳ(ጂ)።
- ተገቢ የሆነ የእይታ አቀራረብ ዘዴ በመለየት የተመረጠ የሥነጥበብ ሥራን ለእይታ ለማቅረብ አዘጋጅ(ጂ)።
- የተመረጠ ጭብጥ/መልእክት ለማስተላለፍ የሥነጥበብ ሥራዎችን በቡድን አውደርእይ/ኤግዚቪሽን አደራጅ(ጂ)።
- ምስል ለየት ያለ ዘዬ እና አንዳች ነገር የሚያሳይ/ስሜት ወይም ሃሳብ ገላጭ መሆኑን ለመወሰን ፣ አወዳድር/ሪ።
- ከሥነጥበብ ሥራ የሚታይ መረጃ በማስደገፍ የግል አተረጓጎምን ደግፍ(ፊ)።
- የግል ሥነጥበብ ሥራ እና በሌሎች የተሠራ ሥራን የግምገማ መስፈርት በመጠቀም አረጋግጥ(ጪ)።

## ሙዚቃ

### የሙዚቃ ትንተናና ምላሽ

- ሙዚቃ በማዳመጥ ልዩነቱን/ለውጡን ገላጭ በሆነ  መልክ/ሁኔታ ማዜም።
- የሙዚቃ ቅላፄን መለያ ባህርይ በመግለጽ/በማሳየት ተገቢ እንቅስቃሴን ፍጠር/ሪ።
- ከበርካታ የሰሜን አሜሪካ ባህሎች ውስጥ መሠረታዊ የሙዚቃ መስሚያ ምሳሌዎችን አስረዳ/ጂ።
- የሙዚቀኞች ሚናዎችን በሰሜን አሜሪካ መለየት እና መግለፅ።
- ምርጥ ስራዎች ደረጃውን ከጠበቀ የሙዚቃ ስነፅሁፍ እንዴት ከልዩ ታሪካዊ ክውነቶች ጋር እንደሚዛመዱ እያዳመጥክ(ሽ) ግለጽ/ጪ።
- ከተለያየ የታሪክ ክፍለ-ዘመን የዓለም ባህሎች የሙዚቃ ዘይቤዎችን እና ልምዶችን የሚወክሉ ምሳሌያዊ ሙዚቃዎችን እያዳመጥክ(ሽ) አስረዳ/ጂ።
- ሁለት ወይም የበለጠ የስነጥበብ ሥራዎችን የሥራዎቹ መሣሪያዎች/እቃዎች (በዜማ ድምፅ፣ በዳንስ ዉስጥ እንቅስቃሴ) ባህርይ ሁኔታዎችን፣ ተመሳሳይ ክዉነት፣ስሜቶችን፣ ወይም ሃሳቦችን ወደ ስነጥበብ ለማሻገር እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አወዳድር/ሪ።

### ሙዚቃ መጫወት

- ከተለያየ ዓለም ባህሎች ጨዋታዎችን እና ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በዝማሬ/በዘፈን/በሙዚቃ አሳይ።
- ከተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች እና ከኣለም ባህሎች፣ የተወሰኑ ከኣጠቃላይ የመማርያ ክፍል ጥናቶች ጋር የተያያዙትን ጨምሮ፣ ዘፈኖችን/መዝሙሮችን እና ዳንሶችን ማቅረብ።

### የሙዚቃ ንባብና ፅሁፍ/ቅኝት

- በትሬብልስታፍ ላይ የሙዚቃ ኖታን /ሶልፌጅዮ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ዘይቤ በመጠቀም ቀላል ጣዕመዜማ  እያነበብክ/ሽ ማሳየት።
- አጭር የቃል ሙዚቃ የድምፅ አወራረድ ሀረግ/አገላለጽን  በሚታወቀው ዓይነት ኖታ አስፍር/ሪ።

### የሙዚቃ ፈጠራ

- በሚታወቁ ጣእመዜማዎች እዚያው በዛው የተፈጠረ ቀላል የሙዚቃ/ተውኔት የድምፅ አወራረድ በተለያየ ሁኔታ በመለዋወጥ በማሳመር ጣዕመዜማ ተጠቀም/ሚ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### የግል እና ማህበራዊ ሃላፊነቶች

- በሰውነት/አካላዊ እንቅስቃሴ ቦታዎች ላይ ከሌሎች ጋር በብቃት የመስራት ችሎታ።
- የማህበርሰባዊነት ስሜትን የሚፈጥር ግኑኝነቶች መገንባት እና ማጠንከር/መጠበቅ።

### የእንቅስቃሴ ክህሎቶች እና እሳቤዎች

- የማይንቀሳቀስ/የማይለዋወጥ እና ተለዋዋጭ  እንቅስቃሴ ሥርዓት/ቅጥ አሳይ/አስረዳ(ጂ)።
- የመከረባበት/የመገለባበጥ ቅደምተከተል ችሎታ አሳይ (በጅምናስቲክስ-እንቅስቃሴ ትምህርት)፡፡
- በተለያየ ዓይነት ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ የመንቀሳቀስ እና ያለመንቀሳቀስ ችሎታ አሳይ።

## የጤና ትምህርት

### ስነ-አመጋገብ እና የአካል ብቃት ***(NF)***

- አልሚ የምግብ ንጥረ ነገሮችን ጥቅም/አሠራር ለይተህ/ሽ መገለጫ ስጥ(ጪ)።
- ስለ ምግብ አወሳሰድ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ እና ክብደትን ስለመቆጣጠር ያለውን ግንኙነት ገልጸህ/ሽ አስረዳ/ጂ።
- ስለ አልሚ ምግብ እና ስለ ሰውነት እንቅስቃሴ ያለውን ግንኙነት አስረዳ/አስረጂ።
- ስለ አሜሪካውያን የአመጋገብ (ለጤና፣ ክብደት ለመቀነስ የሚረዱ ምግቦች) መመሪያ ባጭሩ ጥቀስ/ጥቀሺ።
- ስለ አልሚ ምግቦች እውነታ የሚለጠፍ ምልክት መረጃ ተንትን/ተንትኚ።
- በሰውነት ላይ የሚኖረውን ገጽታ መረጃ ተንትን/ተንትኚ።

### የቤተሰብ ህይወት እና ሰብአዊ ወሲባዊነት፦ **(FLHS)**

- ቤተሰብህ/ሽ እንዴት እንደሚረዱህ/ሽ እና አንተ/አንቺ ቤተሰብህን/ሽን እንዴት እንደምትረዳ/ጂ ለይተህ/ለይተሽ አረጋግጥ/ጪ።